ከዚህ ጋር በተያያዘ ይህንን የመመሪያውን ድንጋጌ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ በሚጠብቅና ሀሳቡ የበለጠ ግልጽ እና የተሟላ በሚያደርግ መልኩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለአለም አቀፍ ግዥ አፈጻጸም በተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ላይም የተካተቱት ድንጋጌዎች ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ እነሱም

13.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቹ ዕቃዎቹንና ተያያዥ አገልግሎቱን የሚያቀርበው ከሀገር ውስጥ ከሆነ ዋጋ ማቅረብ ያለበት በኢትዮጵያ ብር ነው፡፡

13.2 ተጫራቹ ዕቃዎቹንና ተያያዥ አገልግሎቶቹን የሚያቀርበው ከውጭ ሀገር ከሆነ የሚያቀርበው ዋጋ በቀላሉ ሊቀየሩ (ሊለወጡ) በሚችሉ የገንዘብ አይነቶች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ የገንዘብ አይነቶች ማቅረብ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ገንዘብ ውጪ ከሦስት የገንዘብ አይነት በላይ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የድንጋጌዎቹ ዋና መልዕክት ለጨረታ የሚቀርብ ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎት ቦታ ወይም ምንጭ (Source of Origin)ን በመከተል ከውጭ አገር የሚቀርብ ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎት በዓለም ዓቀፍ መገበያያ ገንዘብ፣ እንዲሁም ከአገር ውስጥ የሚቀርብ ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎት ወይም ከግዥው ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጭዎች በኢትዮጵያ ብር ዋጋ ተሞልቶ ለጨረታ ሊቀርብ እንደሚገባ ለማመልከት እንጂ የአገር ውስጥ ተጫራች ከውጭ አገር የሚያቀርበውን ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎት የጨረታ ዋጋ በኢትዮጵያ ብር ብቻ እንዲያቀርብ የማስገደድ አላማ ያለው አይደለም፡፡

በተጨማሪም በዚሁ የጨረታ ሰነድ ክፍል 4 የጨረታ ቅጾች ስር በተዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽም መሰረት ማንኛውም ተጫራች እስከወደብ ድረስ ያሉ ወጪዎችን በFOB (በውጭ አገር ገንዘብ) እንዲሁም ከወደብ መለስ ያሉትን ወጪዎች ደግሞ በኢትዮጵያ ብር በማቅረብ በጨረታ ሊሳተፉ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀበትም ምክንያት ይኸው ነው፡፡

ይሁን እንጂ የሕግ ማዕቀፉ እና የአሰራር ሰነዶቹ ዋና ፅንሰ ሃሳብ ከላይ በተገለጸው መሠረት እንዲፈጸም ለማድረግ ቢሆንም በአፈጻጸም ረገድ በአንዳንድ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች እየተስተዋሉ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እነዚህም፡-

1. አንዳንድ መ/ቤቶች ከመመሪያው እና ከጨረታ ሰነዱ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ጋር በማይጣጣም መልኩ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ሙሉ የመጫራቻ ዋጋቸውን (ከውጭ አገር የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋ ጨምሮ) በኢትዮጵያ ብር ብቻ እንዲያቀርቡ በመጠየቅና በዚህም ምክንያት ከጨረታ ውጭ በማድረግ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ተሳትፎ እንዲቀንስ እየተደረገ ይገኛል፡፡
2. በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአገር ውስጥ ተጫራቾች የመጫራቻ ዋጋቸውን (ከውጭ አገር የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋ ጨምሮ) በኢትዮጵያ ብር ብቻ እንዲያቀርቡ በጨረታ ሰነዱ በተጠየቀው መሠረት ባለማቅረባቸውና ከጨረታ ውጭ በመደረጋቸው ምክንያት ከተጫራቾች ለበርካታ አቤቱታ መቅረብ መነሻ ምክያት ሆኗል፡፡
3. ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ከውጭ አገር ለሚያቀርቡት ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋ በውጭ መገበያያ ገንዘብ ማቅረብ የሚችሉ ሆኖ ሳለ ክፍያው በአገር ውስጥ

ሲፈፀምላቸው በኢትዮጵያ ብር የሚፈፀም በመሆኑ በብርና በውጭ አገር ገንዘብ መካከል የሚፈጠረው የምንዛሪ ልዩነት በአገር ውስጥ ተጫራቾች ላይ ተጨማሪ ኪሳራ ስለሚያስከትል በአገር ውስጥ ተጫራቾች በኩል የመልካም አስተዳደር ችግር የቅሬታ ምንጭ ሆኗል፡፡

4. ከላይ በተገለጹትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በርካታ አቅም ያላቸው አገር በቀል አቅራቢዎች ከጨረታ ውጭ መደረጋቸው ከግዥ መርሆዎች አንዱ የሆነውን ፍትሐዊነት የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች ከላይ የተቀመጠውን የሕግ እና የመደበኛ ጨረታ ሰነዱን መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ በአግባቡ በመረዳት በሚያወጧቸው ጨረታዎች ላይ ፦

1. የአዋጁ፣ የመመሪያውም ሆነ የጨረታ ሰነዱ ድንጋጌዎች የአገር ውስጥ ተጫራቾች ከውጭ አገር የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋ በውጭ መገበያያ ገንዘብ እንዳያቀርቡ የማይከለክሉ መሆኑን፣ ይልቁንም ማንኛውም ዕቃ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ከውጭ አገር የሚቀርቡ እስከሆነ ድረስ ዋጋውን በቀላሉ ሊመነዘር በሚችል ዓለም ዓቀፍ መገበያያ ገንዘብ ማቅረብ እንደሚቻል እና ከአገር ውስጥ የሚቀርብ የዕቃ እና ተያያዥ የአገልግሎት ወጪን ደግሞ በኢትዮጵያ ብር ማቅረብ እንደሚገባ በግልፅ በማሳወቅ፣
2. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እንደተመለከተው የአገር ውስጥ ተጫራቾች ከውጭ አገር የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋ በዓለም አቀፍ ንግድ በስፋት በሚሰራበት የውጭ አገር መገበያያ ገንዘብ ዓይነት እንዲያቀርቡ መፍቀድ፣ እና
3. የውል አስተዳደሩ ላይም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ከላይ በተገለጸው መሰረት ውል በመፈጸምና ክፍያውን በማስተዳደር ፣

በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ተጫራቾች መካከል ፍትሐዊ ውድድር እንዲኖር ፣ ከተጫራቾች ብዛት ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የማሳደግ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የውል አስተዳደር እንዲኖር ተገቢውን በመፈጸም መስሪያቤቶች የበኩላችሁን ኃላፊነት እንድትወጡ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወልደአብ ደምሴ
ም/ዋና ዳይሬክተር

እንዲያውቁት//

ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ገንዘብ ሚ/ር

ግልባጭ

ለመንግስት ግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

መ/ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ